# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.


## ዜና ዘገባ

**ሰኔ 9 ቀን 2004 ዓ.ም**

**የወያኔ ቡድን ከፍተኛ ባለስልጣናት በስርዓቱ ላይ እምነት አጥተው እየሸሹ ነው ተባለ፤**

**በአዲስ አበባ በተከሰተ ግጭት መገናኛ የአኬልዳማ ምድር ሆና አመሸች፤**

**በግጭቱ ብዙ ሰዎች ተገደሉ፤**

**በጎንደርም ሰላም ጠፍቶዋል- ህዝቡም ቆርጦዋል፤**

EthioLion.Com

ከግዜ ወደ ግዜ የወያኔው ቡድን እርስ በርስ ባጋጠመው የውስጥ ችግር ተሰንጎ ...ውጥረት ላይ በመሆኑ እና በውጭ ከተለያዩ ማህበረሰብ ክፍሎች በሚያጋጥመው ተቃውሞ እየተዳከመ መምጣቱን የተረዱ በረሀ አመጣሽ ባለስልጣናቱ ሀገር ጥለው በመጥፋት ላይ መሆናቸው ከተለያዩ አቅጣጫዎች የሚደርሱን ጥቆማዎች አጋለጡ::

ከቅርብ ግዜ ወዲህ ለመለስ ስልጣን ዋነኛ ጠባቂ ናቸው ከሚባሉት የህወሀት የጦር አለቆችና እና የደህንነት ባለስልጣናት መሀከል አንዳንዶቹ ቤተሰብ ለመጠየቅ በሚል ወደ ውጭ ሀገር እየኮበለሉ ለቤተሰቦቻቸው እና ለራሳቸው መጠለያ እያመቻቹ መሆኑን ከተለያዩ አቅጣጫዎች ከሚደርሱ ዘገባዎች ለማወቅ ተችሏል::

ባለፈው ሳምንት ውስጥ የወያኔው ሹመኛ እና በረሀ አመጣሽ የሆነው የቃሊቲ እስር ቤት የበላይ አዛዥ አብርሀም ወ/አረጋይ የተሰኘው ግለሰብ ለቤተሰቦቹ መኖሪያ ለማመቻቸት ወደ አሜሪካ መጓዙን ቅርበት ካላቸው ወገኖች የደረሰነ ዘገባ ይገልፃል::

በአሁኑ ሰዓት በወያኔ ባለስልጣናት መሀከል የተለያዩ ችግሮች ተከስተው እርስ በርስ በውጥረት ላይ ከመሆናቸውም በላይ በተለይ በነባር የህወሀት ባለስልጣናት መሀከል በተፈጠረ መናናቅ ሁሉም የየራሱን ደጋፊ መስርቶ በቃላት እየተፋለመ ከመሆኑም በተጨማሪ ስርዓቱ የወደፊት እጣ ፈንታው አስተማማኝ ባለመሆኑ ከተጠያቂነት ለማምለጥ ሲሉ አስቀድሞ ወደ ተለያዩ ሀገራት ቤተሰቦቻቸውን

ከመላካቸውም በላይ እራሳቸውም እየሄዱ አመቻችተው እየተመለሱ መሆኑን የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል::

የመለስ ቀኝ እጅ የሆኑት የወያኔ የጦር አለቆችና የህወሀት ባለስልጣናት አብዛኞቹ ወደ ውጭ ሀገር ተጉዘው ለቤተሰቦቻቸው እና ለራሳቸው የመኖሪያ ፍቃድ እያመቻቹ መመለሳቸውንና ከእነዚህም ውስጥ ሳሞራ የኑስ ፤ሳዓረ መኮንን ፤ታደሰ ወረደ፤ገዛኢ አበራ እንደሚገኙበት ገልፀዋል::

ይህ በእንዲህ እንዳለ  የወያኔ ቡድን በህዝብ ላይ እየፈጸመ ያለው ግፍ እና መከራ ከዕለት ወደ እለት እየሰፋና እየጨመረ በመምጣቱ ህዝቡ በህብረት እና በአንድነት በመሆን ወያኔን መፋለም በመጀመሩ ግጭቶች በየቦታው እየተቀሰቀሱ መሆኑን ከተለያዩ ከተሞች የደረሰን ዘገባ ገለጸ::

በህዝቡ ላይ የፈጸመው ዘግናኝ ግፍ እያስደነገጠው እና ህዝቡም ቁጣውን እየገለጸ በመምጣቱ የተነሳ በገዛ ጥላው እየደነበረ ባለበት በዚህ ግዜ የህዝቡን ቁጣ ቀስቃሽ የሆኑ እርምጃዎችን በመውሰዱ ከፍተኛ ችግር በተለያዩ ከተሞች ተከስተው ዜጎች እየተገደሉና እየገደሉ እንደሚገኙ የደረሰን ዘገባ ገልጸዋል::

ሐሙስ ሰኔ 7 ቀን 2004 ዓ.ም ከምሽቱ 12 ሰዓት ተኩል ላይ በአዲስ አበባ ከተማ መገናኛ አቅራቢያ በሚገኘው ልዩ ስሙ ጉርድ ሾላ  ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በፖሊስ እና በነጋዴዎች መሀከል በተከሰተ ግጭት እጅግ ቁጥራቸው የበዙ ዜጎች ከፍተኛ ድብደበ የተፈጸመባቸው ሲሆን በፖሊሶች ላይም ከባድ ጉዳት እንደደረሰ ከስፍራው የደረሰው ዜና ይገልፃል::

በመገናኛ አቅራቢያ በሚገኘው በዚሁ ሾላ ገበያ በሚባለው ንግድ ቦታ ላይ በህገ ወጥ ንግድ ስራ ላይ ተሰማተርተዋል በሚል ለብዙ ዓመት ሲሰሩበት ከነበረው ቦታ ላይ ለማፈናቀል ሐሙስ ምሽት ላይ ሊያበርሩዋቸው ሙከራ በማድረጋቸው በተፈጠረ ግጭት የሁለት ሰው ህይወት ወዲያው ሲያልፍ በሌሎች ላይ ከባድ ጉዳት እንደደረሰና በሆስፒታል ህክምና ላይ እንደሚገኙ ከስፍራው ከመጣ ዘገባ ለማወቅ ተችሏል::

በየካ ክፍለ ከተማ ፖሊስ አዛዥ በኮማንደር ማዕረግ ባለው ግለሰብ የተመራው ይሄው ደሀ መንጥር ዘመቻ ላይ የፌዴራል  እና የአዲስ አበባ ፖሊስ በጋራ በመሆን በነጋዴዎቹ ላይ የድብደባ ዘመቻ የከፈቱባቸው ሲሆን ነጋዴዎቹም የሞት ሞታቸውን ከፖሊስ ጋር በመፋለም ላይ እንዳሉ ክርስቲያን ሙስሊም ሳይል በአቅራቢያ ትእይንቱን ሲከታተል የነበረው ህዝብ በሙሉ በፖሊሶች ላይ በድንጋይ እና በዱላ ጥቃት በመሰንዘራቸው የተደናገጡት ፖሊሶቹ  የጥይት እሩምታ ተኩሰው ከፍተው ሁለት ሰዎችን ወዲያው ሲገድሉ ብዙዎችን ማቁሰላቸውም ከአይን እማኞቹ ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል::

ግጭቱ እየተለወጠና ወደ ህዝቡ እየሰፋ መሄዱን የተረዱት የወያኔ ባለስልጣናት ከጃን ሜዳ እና ፈረሰኛ ተብሎ ከሚጠራው ግቢ ሰፍሮ የሚገኘውን የፌዴራል ፖሊስ በአራት መኪና በማስመጣት መንገዶቹን ሙሉ ለሙሉ ዘግተው መኪኖችም ሆነ እግረኛ እንዳይንቀሳቀስ አድርገው በስፍራው የነበሩትን ሁሉ እየጫኑ ወዳልታወቀ ስፍራ እንደወሰዷቸው ታውቋል::

በዕለቱ በተፈጠረው ግጭት ምክንያት በአምስት ፖሊሶች ላይ ከባድ ጉዳት ደርሶባቸው ወደ ፖሊስ ሆስፒታል የተወሰዱ ሲሆን አንደኛው ላይ በደረሰ የከፋ አደጋ ህይወቱ ሳያልፍ እንዳልቀረና በምስጢር የቀብር ስነ ስርዓቱ ሳይከናወን እንዳልቀረ ይገመታል::

ግጭቱ በተከሰተበት አቅራቢያ የሚገኙ ቤቶች በድንጋይ ውርወራ እና በጥይት ተኩስ መስታወቶቻቸው የተሰባበሩ ሲሆን ከምሽቱ 12 ሰዓት ተኩል ጀምሮ እስከ ምሽቱ አራት ሰዓት ድረስ የዘለቀ ትንቅንቅ እንደነበረም በወቅቱ በስፍራው ከነበሩ የዓይን እማኞች የደረሰን ጥቆማ በዝርዝር አስረድቶዋል::

ዜጎች ስራ አጥተው በየሰፈሩ እየተንከላወሱ ባለበት እና በዓለም ላይ የስራ አጥ ዜጎች ቁጥር ከፍተኛ የተመዘገበባት ሀገር በሆነችው ኢትዮጵያ ሰርቼ ልብላ ብሎ በሚዋትት ዜጋ ላይ ዘግናኝ ጭፍጨፋ መፈጸሙ የሚያሳዝን ብቻ ሳይሆን የሚያሳፍር እና የሚያስቆጭ ነው ያሉት የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ወያኔ የሚሉት ቡድን ለቻይናና ለሌሎች ባዕዳን ዜጎች እያጎበደደ ዛሬ እስከ ሱቅ በደረቲነት ስራ ፈቅዶላቸው እንደልባቸው ሲንደላቀቁ በዚህች ሀገር ዜጎች ላይ ግን ይህን የመሰለ ዘግናኝ እርምጃ መውሰዱ የሚያሳዝን ነው ሲሉም በንዴት እና በብስጭት እየገለጹ ይገኛሉ::

በተመሳሳይ ሰሞኑን በአዲስ አበባ ከተማ ኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ቤተል ተብሎ በሚጠራው ሰፈር በህዝቡና በፖሊስ መሀከል በተከሰተ ግጭት የሶስት ሰዎች ህይወት ማለፉን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል::

በአዲስ አበባ ቤተል ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ወያኔ ስልጣን ከመያዙ 20 ዓመት አስቀድሞ የተያዘ የእምነት ይዞታ በኃይል ለመንጠቅ በተደረገ ሙከራ ፖሊስ ከህዝቡ ጋር ፍልሚያ በመጀመሩ ሁለት ፖሊሶች የተገደሉ ሲሆን አንዲት ህጻን ከፖሊስ በተተኮሰ የአስለቃሽ ጥይት ታፍና መሞትዋን ከስፍራው የደረሰን መረጃ አመልክቶዋል::

ማክሰኞ ግንቦት 28 ቀን 2004 ዓ.ም ከቀኑ 4 ሰዓት ጀምሮ የኮልፌ ቀራኒዮ አስተዳዳሪና የክፍለ ከተማው ፖሊስ አዘዥን ጨምሮ በርካታ ባለስልጣናት ተሰባስበው የቤተክርስቲያኑን ይዞታ ለመሸንሸን ሙከራ ባደረጉበት ወቅት በወቅቱ ቤተክርስቲያን በማስቀደስ ላይ የነበሩ ምዕመናን እና ቄሶች በመተባበር ሽንሸናው እንዲያቆም ቢለምኑም ሰሚ አጥተው ይልቁንም በፖሊስ እንዲደበደቡ በመደረጋቸው የተበሳጨው ምዕመን በድንጋይ ባለስልጣናቱንና ፖሊሶቹን እያሩዋሩዋጠ ሲቀጠቅጥ እንደነበር ከዓይን እማኞች የደረሰን ጥቆማ አረጋግጦዋል::

ህዝበ ክርስቲያኑ ከባለስልጣናት እና ከፖሊስ ጋር ሲፋለም የተመለከቱ ሙስሊም ወገኖቹ ከክርስቲያኑ ጋር አብረው በመሆን በፖሊስ ላይ ድብደባና ግድያ የፈጸመ ሲሆን በዋና አስተዳዳሪው እና በፖሊስ አዛዡ ላይ ከባድ ጉዳት እንደደረሰበትም ታውቋል::

በፍርድ ቤት የተያዘን ጉዳይ በእብሪት እና በማን አለብኝነት ተነሳስተው የህዝበ ክርስቲያኑን የአምልኮ ቦታ ለመሸንሸን በኃይል የተጠቀሙት እነዚሁ የወያኔ ባለስልጣናት በፖሊሶቹ ላይ ድብደባው እያየለ መምጣቱን በማየታቸው አጥር እየዘለሉ ለማምለጥ ቢሞክሩም በተለይ ወጣቱ እየተከተለ ከባድ

ጉዳት ያደረሰባቸው ከመሆኑም በላይ የኮማንደር(ኮሎኔል) ማዕረግ ያለው የፖሊስ አዛዡ በድንጋይ ጭንቅላቱን ተመትቶ እራሱን ስቶ ወድቆ እንደነበርም በቦታው ላይ ከነበሩ ሰዎች ለማወቅ ተችሏል::

ከዕለት ወደ ዕለት እብሪት እና ጭካኔያቸው እየጨመረ የመጣው የወያኔ ባለስልጣናት ህዝበ ክርስቲያኑን ቀርበው ማነጋገር እና መተማመን ሲገባቸው በማን አለብኝነት ስሜት ተወጥረው በቤተክርስቲያኑ ቅዳሴ እየተካሄደ ባለበት ወቅት ያለ አንዳች ይሉኝታ እና ሀፍረት ግቢ ድረስ በመግባት መሳሪያ በታጠቁ ፖሊሶች ምዕመናኑን እና ካህናቱን ከማስፈራራታቸውም አልፎ ተርፎ ድብደባ መፈጸማቸው አሳፋሪ ብቻ ሳይሆን አሳዛኝ ፋሽታዊ ተግባር ነው ሲሉ በወቅቱ ግጭቱን ሲከታተሉ የነበሩ የዓይን እማኞች ሲገልጹ ተደምጠዋል::

በወቅቱ አንዲት እናት ህጻን ልጇዋን ለማስቀረብ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበረች እናት ከፖሊስ በተተኮሰ የአስለቃሽ ጥይት ታፍና ህይወትዋ ያለፈ መሆኑንና አምስት ቄሶችም በአስለቃሽ ጥይቱ ታፍነው እራሳቸውን ስተው ቤተ መቅደስ ውስጥ ወድቀው በምዕመናኑ እርዳታ ወደ ውጭ ወጥተው አየር እንዲያገኙ በመደረጋቸው ህይወታቸው ሊተርፍ እንደቻለም የአይን እማኞቹ ገለጻ አስረድቶዋል::

ግጭቱ እየሰፋና ህዝቡም ኃይሉ እየተጠናከረ በመጣበት ወቅት ድንገት ከየት መጣ ሳይባል ከባድ ዶፍ ዝናብ በመዝነቡ ግጭቱ ሊበርድ እንደቻለ ለማወቅ ተችሏል::

በአሁኑ ሰዓት በዕለቱ ከባድ ድብደባ የደረሰባቸው ምዕመናንም በተለያዩ የህክምና ማዕከላት እርዳታ እየተደረገላቸው ሲሆን የፖሊስ አዛዡም በፖሊስ ሆስፒታል ተኝቶ በመታከም ላይ መሆኑን ከአከባቢው የሚገኙ ዜናዎች ይገልፃሉ::

በተያያዘ ዜና በአማራ ክልል ጎንደር ውስጥም ህዝቡ በወያኔ ላይ አምጾ ከባድ ግጭት ተቀስቅሶ ውጥረት ነግሶ መሰንበቱን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገለፀ::በሰሜን ጎንደር በታች አርማጭሆ ወረዳ ሳንጃ ከተማ ፖሊስ እና ህዝቡ መሀከል በተፈጠረ ግጭት በፖሊስ ላይ ከባድ ጉዳት መድረሱን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል::

ከቅርብ ግዜ ወዲህ የወያኔ ቡድን ከጎንደር ለም መሬት ላይ እንደ ገና ዳቦ እየቆረሰ አንዴ ለሱዳን ሌላ ግዜ ለውጭ ባለሀብት እያደለ መሆኑን በመቃወም ቁጣውን እየገለፀ የሚገኘው የጎንደር ህዝብ አሁን አሁን ከወያኔ ታጣቂዎች ጋር ፊት ለፊት ፍልሚያ መጀመሩን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል::

በየጊዜው ለም መሬት ከህዝቡ ላይ እየነጠቀ ለውጭ ሀገር ዜጎች እያደለ ከመሆኑም በላይ የሱዳን ገበሬዎች ወደ ሀገር ውስጥ ዘልቀው ገብተው እንዲሰሩ በመደረጉ በተፈጠረ ግጭት የወያኔው ጦር ጣልቃ ገብቶ የጎንደርን ህዝብ አሳዛኝ በሆነ መልኩ ጭፍጨፋ እየፈጸመበት መሆኑን የተረዱት ዜጎች ጫካ እየገቡ መፋለም መጀመራቸውን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገልጸዋል::

በተለይ አቶ ሽንኩ ከፍያለው እና አቶ ዳኛቸው አያሌው በተባሉት የጎንደር ገበሬዎች መሪነት ከፖሊሶች ጋር ባደረጉት የተኩስ ልውውጥ ከ12 ፖሊሶች በላይ ሲገደሉ ቁጥራቸው ያልታወቀት ደግሞ

EthioLion.Com

ከባድ ጉዳት ያደረሱባቸው መሆኑንና ሁለቱ አዝማቾች ጥይታቸው በማለቁ እራሳቸውን ማጥፋታቸውን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገልጾዋል::

ከግዜ ወደ ግዜ ህዝቡ ወያኔን ለመፋለም ወደ በረሀ እየገባ መሆኑን የተረዱት የወያኔ ባለስልጣናት ጥይት አልቆባቸው እራሳቸውን የገደሉትን ሁለት ሰዎች አስከሬን በመኪና ላይ አስረው መንገድ ለመንገድ እየጎተቱ ህዝቡን ለማስፈራራት ቢሞክሩም እንዳሰቡት ሳይሆን ህዝቡ በሞተ አስከሬን መጫወት ነውር ነው በሚል እንደገና ሌላ ግጭት ተቀስቅሶ ብዙ ሰዎች ጉዳት እንደደረሰባቸው ከስፍረው የደረሰን ዘገባ ገልጾዋል::

ለህዝቡ ሲል እራሱን መስዋዕት ያደረገ ጀግና አስከሬን በየመንገዱ አይጎተትም በሚል ህዝቡ ከወያኔ ተጣቂ ኃይሎች ጋር ግጭት የፈጠረ ሲሆን በዚሁ በተፈጠረ ግጭት የሳንጃ ከተማ እና አካባቢ ነዋሪዎች በውጥረት መሰንበታቸው ታውቀዋል::

በተመሳሳይ በሰሜን ጎንደር ዞን ምዕራብ አርማጭሆ ወረዳ ውስጥ ከመሬት ቆረሳ ጋር ተጀምሮ የነበረው ውጥረት እየከረረ መጥቶ በአሁኑ ሰዓት በዞኑ ውስጥ የጸጥታው ጉዳይ አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱን የደረሰን ዘገባ ገልጾዋል::

ለም መሬት እየተቆረሰ የተሰጣቸው የሱዳን ዜጎች በወረዳው ተወላጆች ላይ በሚወስዱት የኃይል እርምጃ የተነሳ ግጭት ተቀስቅሶ የባለቤትነት ጥያቄን ጭምር ማስነሳቱን ተከትሎ በወረዳው ከፍተኛ ችግር መፈጠሩን ዘገባው ጨምሮ አስረድቶዋል::

ከዜጎች ይልቅ ለባዕዳን የሚያጎበድደው የወያኔ አምባገነን ቡድን በጎንደር ውስጥ ያሉ ለም መሬቶችን ሙሉ ለሙሉ ለባዕዳን ዜጎች እያስረከበ የሀገሬው ተወላጅ እትብታቸው ከተቀበረበት ቀዬ እንዲፈናቀሉና እንዲሰደዱ በማድረጉ የተቆጨ የሀገሬው ተወላጅ ከወያኔ ጋር ግብግብ በመፍጠራቸው በአካባቢው ሰላም ጠፍቶ ውጥረት ነግሶ እንደሚገኝ ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገልጾዋል::

EthioLion.Com